


# መቅድም

ምስጋና ከባሮቹ የሻውን ታጨቐሮ በዕዝነቱ ወደ ኢስላም ለመራው ዕንዲሁም በጥበቡ ኢስላምን ችላ ያለን አጥምሞ በጨለማ ውስጥ ዕንዲዋልል ላደረገው ጌታ ለአላህI ነው::

ሰላምና ዕዝነት በተላኩት አበሳሪና አስጠንቃቂ ፣ በርሱ(በአላህ) ፈቃድ ወደ አላህ ተጣሪ ፣ ዕንዲሁም ለአለም ብርሃን ፈንጣቂ በሆኑት የመጨረሻው መልዕክተኛ በሙሐመድρ ላይ ይሁን::

አላህI ዕንዲህ ይላል :- « ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈፅሞ ከዕርሱ ተቀባይነት የለውም ፣ ዕርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው ::» አል-ዒምራን 85 .

የአለማት ጌታ ጥራት ይገባውና ከኢስላም ውጪ ማንኛውም ሀይማኖት ከንቱ ዕንደሆነና ተቀባይነት ዕንደሌለው ፣ ዕርሱን የተቀበለም ሰው የከሰረና የጠፋ መሆኑን አብራርቷል::

ዕንደሚታወቀው ባለንበት ዘመን አብዛኛው ህዝብ ቀጥተኛውን መንገድ የሳተ አላህንም የካደ ነው ፣ ይህም ማለት የአይሁድ ፣ የክርስትና፣ የቡድሃ፣ የሂንዱና የኮሚኒዝም አማኞች ዕንዲሁም የተቀሩት የባዕድ አምልኮ ተቋዮች ሁሉ ማለት ነው::

አላህI ወደ ኢስላም የመራውና መልካም ዕድል የገጠመው ፣ ዕንዲሁም ዕውነትን ለማብራራት ችሎታ የሰጠው ሰው ኢስላ ምን ሊያደርስላቸው፣ወደርሱም ሊጠራቸው ይገባል:: ይህም በነርሱ ላይ ማስረጃ ዕንዲሆን ምናልባትም ወደ ኢስላም ይገቡ ዘንድ ነው::

አንድ ሰው የመጀመሪያው የዳዕዋ (ሰበካ) ዕርምጃው የሚጣራለትን ዓላማ ማሳወቅ ዕንደመሆኑ ይህ አጭር መፅሐፍ ኢስላምን በማስተዋወቁ ረገድ አጋዥ ይሆናል::አላህI ጭፍን ልቦናን የሚከፍት፣የደነቆረ ጆሮን የሚያሰማ፣የታወረ ዓይንን የሚያበራ ዕንዲያደርገውና ፍሬያማ ዕንዲሆን ዕንመኛለን::

ይህ አጭር መፅሓፍ ለአዳዲስ ሙስሊሞች ስለ ሃይማኖታቸው አጠር ባለ መልኩ ትክክለኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚረዳ ነው::ይህም በአላህ ፈቃድ ዕስልምናቸው ያማረ ዕንዲሆን በርሱም ላይ ዕንዲፀኑ በኢስላማዊውም ጥሪ በመሳተፍ ኢስላምን በአካባቢያቸው ላሉ ሰዎች ዕንዲያደርሱ አስተዋፅኦ ያደርጋል::የዳዕዋንና የትግልን ባንዲራ ዕንዲያነግቡ ያግዛቸዋል::ፀጋ በአላህI ዕጅ ነው::ለፈለገው ይሰጠዋል::

ምስጋና ለዓለማት ጌታ ለአላህI ነው !!

በመዲና ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ
የጥናትና የምርምር ማዕከል



# ስለ ኢስላም አጭር ማብራሪያ

*ምስጋና ለአለማት ጌታ ለአላህ የተገባ ነው:: የአላህ ሰላምና |ዕዝነት የመልዕክተኞች መሪ በሆኑት ነብይ በሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን::*

ኢስላም ማለት ***«ከአላህ ሌላ በሀቅ የሚመለክ ጌታ የለም፣ሙሐመድ*** ρ ***የአላህ መልዕክተኛ ናቸው»*** ብሎ በልቦና ማመን፣ በአንደበት መመስከርና በተግባርም ማረጋገጥ፣በስድስቱ የኢማን መሰረቶች ማመንና አምስቱን የኢስላም መስረቶች መፈፀም ዕንዲሁም ይህንኑ ስራ ባማረ መልኩ መፈጸምን(ኢህሳንን) ያጠቃልላል::

ኢስላም ፤ አላህ የነብያትና የመልዕተኞች (ሩሱሎች) መደምደሚያ በሆኑት በዓብደላህ ልጅ ሙሐመድρ ላይ ያወረደው የመልዕክቶቹ ሁሉ መቋጫ ነው:: አላህ ዘንድም ከኢስላም በቀር ተቀባይነት ያለው ሀይማኖት የለም:: ይህንን ዕውነተኛ ሀይማኖት አላህI ገርና ቀላል፣ አዳጋችም ሆነ አሰቸጋሪ ነገር የሌለበት አድርጎታል:: አማኞችን ከአቅም በላይ የሆነ ትዕዛዝ አላዘዛቸውም:: የማይችሉትንም ግዴታ አላደረገባቸውም:: ኢስላም መሰረቱ የአላህ አንድነት፣ መለያው ዕውነተኝነት፣ ዛቢያው ፍትህ ፣ መነሻው ሀቅና ዕዝነት ነው:: ኢስላም ሰዎችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ሆነ ለዓለማዊ

ኑሯቸው ጠቃሚ ወደ ሆነ ነገር ሁሉ የሚመራ፣ በአንፃሩም ጎጂ ከሆነ ነገር ሁሉ የሚያስጠነቅቅ ታላቅ ሀይማኖት ነው::

ኢስላም አላህI የሰው ልጆችን ዕምነትና ባህሪ ያስተካከለበት፣ የዱንያንና የአኺራን ህይወት ያሳመረበት፣ የተራራቁ አመለካከቶችንና የተለያዩ ዝንባሌዎችን አንድ በማድረግ ከንቱ ከሆነ ፅልመት አጥርቶ ወደ ዕውነት የመራበት ሀይማኖት ነው:: አጠቃላይ ህግጋቱም ሆነ መልዕክቶቹ ፍፁም በሆነ መልኩ ተብራርተዋል:: ኢስላም ሀቅን ዕንጂ አልተናገረም! በዕውነትና በፍትህ ዕንጂ አልፈረደም! ትክክለኛ ዕምነትን፣ ቀና የሆነ ተግባርን፣ የላቀ ባህሪን ዕንዲሁም ታላቅ ስርዓት ን አስተምሯል::

**የኢስላም መልዕክት የሚከተሉትን ዓላማዎች ያካትታል:-**

**1-** የመጀመሪያው ዓላማው የሰው ልጆችን ከፈጣሪያቸው ጋር ማስተዋወቅ ሲሆን ያማሩ ስሞቹ ወደር ዕንደሌላቸው ፣ መልካም ባህሪያቱ ምሳሌ ዕንደሌላቸው ፣ በጥበብ የተሞሉ ስራዎቹንም ማንም ዕንደማይጋራው፣ ዕንዲሁም አምልኮ(ዒባዳ) ለርሱ ብቻ ዕንደሚገባ በዚህም ቢጤ ዕንደሌለው ያስተምራል::

**2-** የሰው ልጆች አላህ በቁርኣንና በሀዲስ የደነገጋቸውን በዱንያም ሆነ በአኺራ ታላቅ የሚያደርጋቸውን ትዕዛዛቱን ዕንዲፈጽሙ፣ ከከለከላቸውም ነገሮች ዕነዲቆጠቡ፣ በዚህም አጋር የሌለውን አላህን ብቻ ዕንዲያመልኩ ይጣራል::

**3-** ከሞት በኋላ የሚኖራቸውን ዕጣታ፟ጁን በቀብር ውስጥ የሚያጋጥማቸውንም፣ ሁኔ በትንሳኤ ቀን ያለውን ክስተትና አላህም ዕንደሚተሳሰባቸው ዕንዲሁም የመልካም ስራ ዋጋ መልካም፣ የክፉ ስራ ምንዳም ክፉ መሆኑንና ዕንደየስራቸውም መጨረሻቸው ወደ ጀነት ወይም ወደ ዕሳት ዕንደሚሆን ያስገነዝባቸዋል፡፡

| ከዚህ በመቀጠል ዋና ዋናዎቹን የኢስላም መርሆዎች አጠር ባለ መልኩ ለማብራራት ዕንሞክራለን፡፡

# አርካነል ኢማን (የዕምነት ማዕዘናት)

**1-በአላህ ማመን-** በአላህ ማመን የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል::

1.1- በአላህ ጌትነት ማመን:- አላህ ፈጣሪ ጌታና የሁሉ ነገር ባለቤት ዕንደሆነ፣ የፍጡራንን ዕንቅስቃሴዎች በሙሉ ዕንደሚያስተናብርና በነርሱም ላይ ሙሉ ስልጣን ዕንዳለው ማመን ነው::

1.2- በአላህ ብቸኛ ተመላኪነት ማመን:- አላህ ዕውነተኛ አምላክ ዕንደሆነና ከርሱ ሌላ የሚመለክ ማንኛውም አካል ከንቱ ዕንደሆነ ማመን ነው::

1.3- በአላህ ስሞችና ባህሪያት ማመን:- በቁርኣንና በሀዲስ በተገለፀው መሰረት አላህ መልካም ሰሞችና የላቁ ምሉዕ የሆኑ ባህሪያት ዕንዳሉት ማመን ነው::

**2-በመላዕክት ማመን-**መላኢኮች ዘውትር አላህን የሚገዙ፣ ለትዕዛዛቱም ተገዢ የሆኑ አላህ የፈጠራቸው የተከበሩ ባሮቹ ናቸው:: አላህ የተለያየ የስራ ድርሻ ሰጥቷቸዋል:: ከነርሱ መካከል ጂብሪል የተባለው የወሕይ (ከአላህ ወደ ነብያት የሚወርድ መልዕክት) ወኪል ሲሆን ከነብያትና ከሩሱሎች አላህ ወደሻው የወሕይን መልዕክት ይዞ ይወርዳል:: ሚካል(ሚካኢል) የተባለው መልዐክ ደግሞ ለዝናብና ለተክሎች የተመደበ ነው:: ኢስራፊል ደግሞ በዓለም ጥፋትና በትንሳኤ ቀን በቀንድ ለመንፋት ተመድቧል::

እንዲሁም መለኩልመውት የተባለው መልዐክ በሞት ጊዜ ነፍስን ለማውጣት ተመድቧል::

**3-በመፅሐፍት ማመን-** አላህ በመልዕክተኞቹ ላይ ቅን መመሪያ፣ ፀጋና ተሀድሶን ያዘሉ መፅሐፍትን አውርዷል:: ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉትን ዕናውቃለን::

/ ተውራት- አላህ በነብዩ ሙሳ϶ ላይ ያወረደው ሲሆን ለኢስራኤል ልጆች ከተሰጡት ታላላቅ መፅሐፍት አንዱ ነው::

/ ኢንጂል- አላህ በነብዩ ዒሳ϶ ላይ ያወረደው መፅሐፍ ነው::

/ ዘቡር- አላህ ለነብዩ ዳዉድ϶ የሰጠው ነው::

/ ሱሑፍ- ለነብዩ ኢብራሂም϶ የተሰጠ ነው::

/ ታላቁ ቁርኣን- አላህ በመጨረሻው ነብይ በሙሐመድρ ላይ ያወረደው ሲሆን ከርሱ በስተፊት የነበሩ መፅሐፍትን በሙሉ አላህ በርሱ ሽሯል:: ቁርኣን ዕስከ ዕለተ-ትንሳኤ በፍጡራን ላይ በአጠቃላይ ማስረጃ ሆኖ ስለሚኖር የጥበቃውን ዋስትና አላህ ወስዷል::

**4-በሩሱሎች(በመልዕክተኞች) ማመን-** አላህ ወደ ፍጡራን መልዕክተኞችን ልኳል:: የመጀመሪያው ኑህ϶ ሲሆኑ የመጨረሻው ደግሞ ሙሐመድρ ናቸው:: የመርየም ልጅ ዒሳንና ዑዘይርን ጨምሮ (የአላህ ሰላምና ዕዝነት በነርሱ ላይ ይሁን) ሰው የሆኑ ፍጡራን ናቸው:: የአላህን ብቸኛ ጌትነት የሚያጋራቸው ምንም ዓይነት መለኮታዊ ባሕሪ የላቸውም:: አላህ ከባሮቹ መካከል መልዕክት አድራሾች በማድረግ አክብሯቸዋል::አላህም መልዕክቱን በሙሐመድρ ላይ ባወረደው ዘልዓለማዊ ኪዳን ደምድሟል::ለሰው ዘር

በሙሉም ልኳቸዋል፡፡ ከርሳቸው በኋላ ነብይ የለም፡፡

**5-በመጨረሻው ቀን ማመን-** የመጨረሻው ቀን አላህ ፍጥረታትን በሙሉ የሚሰበስብበት፣ የሰው ልጆችን ታላቅ ተድላ ወይም አሳማሚ ቅጣት ባለበት ዓለም ዕንዲኖሩ ከመቃብራቸው ሕያው አድርጎ የሚያስነሳበት ቀን ነው፡፡ በመጨረሻው ቀን ማመን ከሞት ኋላ ባሉ ክስተቶች በሙሉ ማመንን ያካቷል፡፡ ይህ ም በቀብር ፈተና፣ በውስጡ ባለው ጸጋና ቅጣት ከዚያም በኋላ በሚከሰተው ዕንደ ትንሳኤ፣ መሰብሰብና መመርመር ዕንዲሁም ጀነትና ጀሀነም ውስጥ ባለው ሁሉ ማመንን ያጠቃልላል፡፡

**6-በቀደር(በውሳኔ) ማመን-** በቀደር ማመን ማለት አላህ] ቀድሞ ባወቀውና ጥበቡ በፈረደው መሰረት ክስተቶችን ዕንደወሰነ በዚሁም መሰረት ፍጡራንን ዕንዳስገኘ ማመን ነው፡፡ አላህ ዘንድ ሁሉም ነገር ጥንቱኑ ቋወቀ ነው፡፡ በተጠበቀው ሰሌዳም የሰፈረ ነው፡፡ አላህ ሁሉንም በፍላጎቱ ፈጥሯል፡፡ በአላህ ፍላጎት፣ ክዋኔና መፍጠር በቀር የሚከሰት ነገር የለም፡፡

! ! ! ! !

# አርካኑል ኢስላም (የኢስላም ማዕዘናት)

ኢስላም በአምስት መሰረቶች ላይ የተገነባ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ትክክለኛ ሙስሊም ሊሆን የሚችለው በነርሱ አምኖ ተግባራዊ ሲያደርጋቸው ብቻ ነው፡፡ ዕነርሱም :-

**1-** *«ላ ኢላሀ ኢልለላህ ሙሐመዱን ረሱሉላህ»* (ከአላህ በቀር አምላክ የለም፡ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው) ብሎ መመስከር ነው፡፡ ይህች የምስክርነት ቃል ወደ ኢሰላም መግቢያ ቁልፍ ናት፡፡ ኢስላምም የሚገነባው ዕርሷን መሰረት አድርጎ ነው፡፡ አላህ ዕውነተኛው አምላክ ነው፡፡ ከርሱ በቀር ያሉ አማልክት በሙሉ ከንቱ ናቸው፡፡ «ኢላህ» ማለት «መዕቡድ» ወይም የሚመለክ ማለት ነው፡፡

በነብዩ ሙሐመድρ መልዕክተኛነት ማመን ማለት ደግሞ ነብዩρ የተናገሩትን ዕውነት ብሎ መቀበል፣ ያዘዙትን ታዘዝ፣ ያወገዙትንና የከለከሉትን መከልከል ዕንዲሁም አላህን ዕርሳቸው በደነገጉት መሰረት ብቻ ማምለክ ማለት ነው፡፡

**2-** ሰላት:- በቀንና በማታ አምስት ጊዜ የሚፈፀሙ አምስት ሰላቶች(ስግደቶች) ናቸው፡፡ አላህ በባሮቹ ላይ ያለውን ሀቅ ዕንዲወጡ፣ ለፀጋዎቹም ምስጋና ዕንዲያደርሱና ከአፀያፊና ከተጠላ ተግባር ከልካይ ዕንዲሆንላቸው ሰላትን ደንግጎላቸዋል፡፡ ሰላት

ከዝሙትና ከፀያፍ ተግባር ሁሉ ይጠብቃል:: በአንድ ሙስሊምና ቋቁው መካከል አገናኝ ስለሆነ ሙስሊም በሰላቱ ወቃስፎን ጌ ይማፀናል:: በሚስጥርም ወደርሱ ይፀልያል::

አላህም የሃይማኖት ፅድቀት የኢማን ጥንካሬ ዕንዲሁም ቅርብና ሩቅ መልካም ምንዳ ሰላትን ተከትሎ ዕነዲመጣ አድርጓል:: መልካም ምንዳንም ያስገኛል:: ዕንዲሁምታላቅ አካላዊና መንፈሳዊ ዕርካታን ይሰጣል:: ከዚህም ባሻገር በዱንያም ሆነ በአኺራ ስኬታማ ያደርጋል::

**3-** ዘካ:- ዘካ ማለት ግዴ የሆነበት ሰው በየአመቱ ለሚገባቸው ችግረኞችና ለሌሎች ዘካ ዕንዲወስዱ ለተፈቀደላቸው ሰዎች የሚከፍለው ሰደቃ(ምፅዋት) ነው:: የዘካን ኒሷብ(ዘካ ግዴ የሚሆንበት አነስተኛው የገንዘብ መጠን) የደረሰ ገንዘብ በሌለው ሰው ላይ ታግደአይሆንም:: ግዴታ የሚሆነው በባለሀብቶች ላይ ሲሆን ይህም ሀይማኖታዊ ግዴታቸውን ዕንዲወጡና ኢስላማዊ ባህሪ በውስጣቸው ዕንዲያብብ ነው:: ዕንደዚሁም ዘካ በአንድ ሙስሊምና በንብረቱ ላይ ሊደርሱ ከሚችሉ ጥፋቶች ይከላከላል:: ከፈፀመው ወንጀልም ያፀዳዋል:: ለችግረኞቸና ዕርዳታ ለሚሹ ወገኖች ድጋፍ ይሆናል:: ብሎም ለማህበራዊ ችግሮች መፍትሄ ይሆናል:: ከመሆኑም ጋር ይህ ምፅዋት (ዘካት) ለባለሀብቶች አላህ ከሰጣቸው ገንዘብና ንብረት ጋር ሲነፃፀር በጣም ጥቂት ነው::

**4-** ፆም:- ፆም ማለት በየአመቱ ዕንደ ጨረቃ አቆጣጠር በዘጠነኛው ወር የተከበረውን ወርሃ ረመዳን መፆም ነው:: በረመዳን በየቀኑ ጎህ ከቀደደበት ጊዜ ጀምሮ ጀምበር ዕስክትጠልቅ ባለው ጊዜ በኢስላም ከተወሰኑ አንዳንድ ታቁሰረ

ፍላጎቶች:- ከምግብ፣ መጠጥና ስጋዊ ተራክቦ በመቆጠብ የአለም ሙስሊሞች በሙሉ በአንድ አይነት ሁኔ ይፆሙታል:: አላህም በዚህ መልካም ተግባራቸው ከችሮው በጎ በመዋልና ኢማናቸውን በመሙላት ይክሳቸዋል:: ወንጀላቸውን ይምርላቸዋል::ዕርሱ ዘንድ ያላቸውን ደረጃ ከፍ ያደርግላቸዋል:: ዕንዲሁም አላህ ለፆመኞች ካዘጋጀው የዱንያና የአኺራ መልካም ነገር ሁሉ ይቸርላቸዋል::

**5-** ሐጅ:- ሐጅ ማለት ወደ ተከበረው የአላህ ቤት(ካዕባ) ለየት ያለ ዒባዳ(አምልኮ) ለመፈፀም በተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚደረግ ጉዞ ነው:: ሐጅ በኢስላም ታላቅ ቦታ ያለው ዒባዳ ነው:: አላህ አቅም ባለው ሰው ላይ በሕይወቱ አንድ ጊዜ ግዴታ አድርጎታል:: ለሐጅ ስነስርዓት ሙስሊሞች ከመላው ዓለም በምድር ላይ ተመራጭና ቅዱስ በሆነው ስፍራ ይሰባሰባሉ:: አንድ ዓይነት ልብስ በመልበስ አንዱን አምላካቸውን ይገዛሉ:: በመሪና በተመሪዎች ፣ በሀብታምና በድሃ፣ በነጭና በጥቁር መካከል ልዩነት የለም:: በጊዜኗታ በቦ የተወሰኑ የሐጅ ሰራዎችን በአንድነት ያከናውናሉ::ከዋና ዋናዎቹ የሐጅ ተግባራት መካከል በዓረፋ መቆም፣ በተከበረው ካዕባ ዙሪያ ጠዋፍ ማድረግ፣ ሰፋና መርዋ በተባሉት ተራራዎች መካከል መሮጥ ይገኙታል:: ሐጅ ለመቁጠርና ለመዘርዘር የሚያዳግቱ ዕጅግ ብዙ ሀይማኖታዊና ማሕበራዊ ጥቅሞች አሉት::

! ! ! ! !

# *አል-ኢህሳን*

ኢህሳን ማለት በልቦናና በተግባር አላህን ዕንደምታየው አድርገህ ማምለክ ነው፡፡ አንተ ባታየው ዕርሱ ያይሃልና! ይህንን በልቦና በማሳደር በነብዩρ ሱና መሰረት ዒባዳን መከወን ፈለጋቸውንም አለመፃረር ኢህሳን ነው፡፡

~ ~ ~ ~ ~

ከዚህ በላይ ስለኢስላም፣ ኢማንና ኢህሳን የሰፈረውን አጠር ያለ ማብራሪያ «***ኢስላም***» የሚለው መጠሪያ ያካትተዋል፡፡

ዕንደሚታወቀው ኢስላም የግለሰቦችንም ሆነ የኢስላምዊ ማህበረሰቦችን ሕይወት በዱንያም ሆነ በአኺራ ለስኬት በሚያበቃቸው መልኩ ስርዓት አስይዟል፡፡ ለምሳሌ፡- ትዳርን ፈቀደ፡ አበረታታም፡፡ በአንፃሩም ዝሙትንና ግብረ-ሰዶማዊነትን ዕንዲሁም መሰል ፀያፍ ተግባራትን ከለከለ፡፡ ዝምድናን መቀጠልን፣ ለድሆችና ለችግረኞት ማዘንንና መንከባከብን ግዴ አደረገ፡፡ መልካም ፀባይን ሁሉ አስተማረ፡፡ ከመጥፎ ፀባይም ሁሉ በመከልከል አስጠነቀቀ፡፡ ለተከታዮቹም ከንግድ፣ ከኪራይና ከመሳሰሉት የገቢ ምንጮች የሚገኘን ጥቅም ፈቀደ፡፡ ወለድንና ክልክል የሆኑ

ማጭበርበርና ቃሽል ያለባቸውን የንግድ ዘርፎች በሙሉ ዕርም አድርጓል::

ሰዎች ለህግጋቱ ከመገዛትና የሌሎችን መብት ከመጠበቅ አኳያ ዕንደሚለያዩ ከግምት ውስጥ በማስገባት ዕንደ «ሪዳህ»(ኢስላምን ክዶ መውጣት)፣ ዝሙት ፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣትና በመሳሰሉት የአላህን ሕግጋት በመጣስ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ላይ ከበድ ያለ ቅጣት ደንግጓል:: ዕንዲሁም በሰዎች ደም፣ ንብረትና ክብር ላይ በሚፈፀሙ ዕንደ ግድያ፣ ስርቆት፣ ስም ማጥፋት፣ ድብደባና የሰዎችን ንብረት ያለአግባብ መውሰድ በመሳሰሉ ወንጀሎች ላይ ገሳጭ ቅጣቶችን ደንግጓል:: ቅጣቶቹም ከወንጀሉ ክብደትና ቅለት ጋር ተመጣጣኝነት ያለው ሲሆን በደልም ሆነ ቸልተኝነት የለበትም::

ዕንደዚሁም ኢስላም በገዢና በተገዢ መካከል ያለውን ግንኙነት በመወሰን አስተዳደርን ስርዓት አስይዟል:: ተገዢው ሕዝብ ወንጀል ነክ ባልሆነ ነገር በሙሉ ለገዢው መደብ ታዛዥ ዕንዲሆን ግዴታ አድርጓል:: በግለሰቦችና ባጠቃላይ ማሕበረሰቡ ላይ በሚያስከትለው መዘዝ ሳቢያ አመፅን ከልክሏል::

! ! ! ! !

በመጨረሻም ይህችን አጠር ያለች መልዕክት በዚህ ማጠቃለያ ሀሳብ ዕነቋጫለን፡፡

ኢስላም በሰው ልጆችፏቸወፀጄ በግለሰቦችና በሚኖሩበት ማህበረሰብ መካከል በሁሉም መስክ ትክክለኛና መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ያስችላል፡፡ መልካም ባህሪንና ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነትን ለተከታዮቹ አስተምሯል፡፡ በአንጻሩም መጥፎ ከሆነ ባህሪና ሻካራ ከሆነ ግንኙነት ቀዞዮቹን አስጠንቅቋል፡፡ ይህም የኢስላምን ምሉዕነትና በሁሉም ጎኑ ለሰው ልጆች የሚበጅ ዕንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

*<u>ምስጋና ለዓለማት ጌታ ለአላህ የተገባ ነው !</u>*